## ከምዕራፍ አንድ (የከተማችን መገኛ) የወጡ የክለሳ ጥያቄዎች

## ክፍል ሁለት

### ክፍል አንድ ምርጫ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. አቅጣጫን በቃላት ለመግለጽ ከሚከተሉት ውስጥ ጥቅም ላይ የማይውለው የትኛው ነው?

   ሀ. በስተግራ    ለ. በስተጀርባ    ሐ. ከላይ    መ. መስፈርት

2. ከአዲስ አበባ በስተሰሜን የሚገኘው ተራራ የትኛው ነው?

   ሀ. ዝቋላ    ለ. እንጦጦ    ሐ. መነጋሻ    መ. ኤረር

3. አዲስ አበባ በኢትዮጵያ ውስጥ ያላት ፍጹማዊ መገኛ በየትኛው ንፍቀ ክበብ ነው?

   ሀ. በምዕራብና በደቡብ    ለ. በሰሜንና በምሥራቅ

   ሐ. በደቡብና በምሥራቅ    መ. በሰሜንና በምዕራብ

4. ካርታን ለመሳልና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የግድ የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

   ሀ. ቀለም    ለ. መስፈርት (Scale)

   ሐ. ብዕር    መ. ወረቀት

5. ኬንትሮስን በመጠቀም ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ማወቅ ይቻላል?

   ሀ. ሰዓትና ጊዜን    ለ. ሙቀትን

   ሐ. ከፍታን    መ. ዝናብን

LIVEWORKSHEETS

6. የአንድን ቦታ መገኛ "ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጀርባ" ብለን ብንገልጽ የትኛውን የመገኛ መንገድ ተጠቀምን?

ሀ. ፍጹማዊ መገኛ ለ. ኬክሮሳዊ መገኛ

ሐ. አንጻራዊ መገኛ መ. ኬንትሮሳዊ መገኛ

7. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ትልቁ የገበያ ማዕከል ማን ይባላል?

ሀ. ቦሌ መድኃኒዓለም ለ. መርካቶ

ሐ. ካዛንቺስ መ. ላፍቶ

8. 90 ዲግሪ ($90^{\circ}$) የኬክሮስ መስመር የሚያመለክተው የትኛውን ነው?

ሀ. የምድር ወገብን ለ. ዋልታዎችን

ሐ. ትልቁ ሜሪዲያንን መ. መስፈርትን

9. ከአዲስ አበባ ወደ ባህር ዳር ከተማ ለመጓዝ የትኛውን አቅጣጫ መከተል ይኖርብናል?

ሀ. ደቡብ ለ. ምሥራቅ

ሐ. ሰሜን መ. ምዕራብ

10. በካርታ ላይ የሚገኙ የተለያዩ ምልክቶች (ለምሳሌ፡ የተራራ፣ የወንዝ) ምን ይባላሉ?

ሀ. የካርታ ቁልፍ (Legend) ለ. የካርታ ርዕስ

ሐ. የካርታ አቅጣጫ መ. የካርታ መስፈርት

LIVEWORKSHEETS

**ክፍል ሁለት፡** የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀስተ በማለት መልሱ

1. አቅጣጫን ለማወቅ ኮምፓስ (Compass) መጠቀም እንችላለን።
2. ኬክሮስና ኬንትሮስ ምድር ላይ በትክክል ያሉ የሚታዩ መስመሮች ናቸው።
3. አዲስ አበባ የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማም ናት።
4. ካርታ በትክክል ለመሳል የመሬትን ገጽታ ማሳነስ አያስፈልግም።
5. የምድር ወገብ (Equator) ምድርን ለሁለት እኩል (ሰሜንና ደቡብ) ይከፍላል።
6. ፍጹማዊ መገኛ ከአንጻራዊ መገኛ የበለጠ ትክክለኛ ቦታን ለመጠቀም ይረዳል።
7. አዲስ አበባ በቆላማ የአየር ንብረት ውስጥ ትገኛለች።
8. ትልቁ ሜሪዲያን (0 ዲግሪ ኬንትሮስ) የሚያልፈው በእንግሊዝ ግሪንዊች ከተማ በኩል ነው።
9. በካርታ ላይ ሰሜን አቅጣጫ ሁልጊዜ ወደ ታች ነው የሚመለከተው።
10. አዲስ አበባ በ 1879 ዓ.ም በአጼ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ተመሠረተች።

LIVEWORKSHEETS